Safe retrieval & Disposal of needles and syringes – Amharic

# መርፌንና ስይሪንግስ በጥንቃቄ መጠቀምና መጣል

መስከረም/September 2003

***ለኤድስ/AIDS ምክንያት ለሆነው በኤችአይቪ/HIV ቫይረስ ለመያዝ ወይም በመርፌና ስይሪንጅ አማካኝነት በደም ለሚተላለፉ ቫይረሶች በርስዎ ላይ ችግሩ በጣም አነስተኛ ሊሆን ይችላል።***

**የወደቀ መርፌና ስይሪንጅ ሲያገኙ ምን እንደሚያደርጉ**

መርፌውንና ስይሪንጁን እርስዎ ለማስወገድ ካልፈለጉ ወይም አስፈሪና አስቸጋሪ ቦታ ከሆነ በ24 ሰዓት መረጃ መስጫ የርዳታ መስመር ላይ በመደወል እንዲነሳ ቅንጅት ለማድረግ ይቻላል።

**Disposal Help-line**
**1800 552 355**

## ወይም

እርስዎ የሚያነሱት ከሆነ:

- ለስላሳ ጎማ ወይም የፕላስቲክ ጓንት ለመከላከያ ማድረግ። ወፈር ያለ ጓንት እንደ የአትክልተኛ ጓንት ማድረግ መርፌንና ስይሪንጉን ለመልቀም ያስቸግራል።
- ተቀባይነት ያለው ማጠራቀሚያና ክዳን ወደ ቦታው መውሰድ ያስፈልጋል። እነዚህ ማጠራቀሚያዎቸ በአብዛኛው ምክር ቤትና የመርፌና ስይሪንጅ ፕሮግራም ይገኛል። ምንም ከሌለዎት ጠንከር ያለ የፕላስቲክ ማጠራቀሚያ እንደ ዲተርጀንት ጠርሙስ መጠቀም። የብርጭቆ ጠርሙሶች ስለሚሰበሩ **አለመጠቀም።**
- ለመድረስ ካስቸገረ በጥንቃቄ ቆሻሻና ሌሎች ነገሮችን ከአካባቢው በማስወገድ በቀጥታ ማንሳት ይችላሉ
- በከዘራ ወይም መጥረጊያ እጀታ ጫፍ ከአንድ በላይ የሆኑ መርፌና ስይሪንጅ ማላቀቅ ይቻላል። ይህንን በጥንቃቄ **ማካሄድ** ይሆናል። ከዚያ ለእያንዳንዱ መርፌና ስይሪንጅ ማንሳትና መሰብሰብ ይቻላል።
- መርፌና ስይሪንጅ ያለውን በርሜል ለመሰብሰብ በፕላስቲክ ጫፉ ማንሳት። በመርፌው ጫፍ **አለማንሳት።** የመርፌው ጫፍ ከርስዎ መራቁን ያርጋግጡ።
- ምንም እንኳን ክዳኑም ቢጣል መርፌንና ስይሪንጅን እንደገና ክዳኑን **አለመጠቀም።**
- በማጠራቀሚያ ሲጣል የመርፌንና ስይሪንጅን ጫፉ ማስቀደም። ማጠራቀሚያው በአንድ ቦታ መቀመጥ ሲኖርበት በእጅ አለመያዝ።
- ክዳኑን በማጠራቀሚያው ማስቀመጥ።
- የእጅ ጓንቱን በፕላስቲክ ከረጢት ማጠራቀም ይሆናል። የፕላስቲክ ከረጢቱን ጫፉን ማሰርና በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ መክተት።
- እጆችን በሳሙናና በወሃ መታጠብ።
- ማጠራቀሚያውን ለመጣል ወደ አካባቢ የመርፌና ስይሪንጅ ፕሮግራም፥ የአካባቢ ምክር ቤት ወይም ለመጣል እርዳታ መስጫ መስመር በበለጠ ምክር ማግኘት። መርፌንና ስይሪንጅን በቆሻሻ ማጠራቀሚያ፥ በፍሳሽ ቦይ ወይም ሽንት ቤት አለመጣል።

**በመርፌ በመወጋት ከተጎዱ ምን እነደማደረግ**

በወደቀ መርፌና ስይሪንጅ ከተወጉ ከዚህ የሚከተለው እርምጃ መወሰድ አለበት(ብዙ ጊዜ በመርፌ መወጋት ጉዳት ተብሎ ይጠራል):

- በአካባቢው ውሃ ማፍሰስ
- ቁስሉን በሙቅ ውሃና በሳሙና በደንብ ማጠብ
- በቁስሉ ላይ አንቲሰብቲክ ማድረቂያ ማድረግና ውሃ በማያስገባ ፋሻ ማሰር
- ቁስል እንዳይፈጥርና ተገቢውን ህክምና መከታተል እንደማያስፈልግ ይሆናል።
- መርፌና ስይሪንጁን ለመልቀም ካልተቻለ በአካባቢው ምልክት በማድረግ በሌሎች ላይ ችግር እንዳይፈጥር ማድረግና የርዳታ መስመርን ማናገር ይሆናል።